Washington State Health Care Authority

የግላዊ ድርጊቶች ማሳወቂያ

ጥቅምት 2015

ይህ ማስታወቂያ የዋሽንግተን ግዛት ጤና ጥበቃ ባለስልጣን (HCA, እኛ ወይም እኛ) ስለ እርሶ የጤና መረጃ እንዴት እንደሚጠቀም ወይም እንደምንጠቀም እና ይህንን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደምትችሉ የሚገልፅ ነው፡፡ ***እባክዎን በጥንቃቄ ይመልከቱ***

ይህ ማስታወቂያ እየተሰጠት ያለው HCA በህጉ የእርሶን መረጃ ምስጢራዊነት የመጠበቅ እና ይህንን ማስታወቂያ ለጤና ጥበቃ ባለስልጣን ደንበኞች ሁሉ መስጠት ስለሚጠበቅበት ነው፡፡ በእርሶን የአገልግሎት ወይንም ሽፋን ተጠቃሚነት ብቃት ላይ ጫና አያሳድርም፡፡

ማጠቃለያ

የእርስዎ መብቶች	የእርስዎ ምርጫዎች	የእኛ አጠቃቀም እና ይፍ አደራረግ
እርስዎ የሚከተሉት መብት አልዎት፡	**እኛ ስለምናጋራው የጤና መረጃ በተመለከተ ምርጫዎን ሊነግሩን ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንዴት እንደምናደርግ፡**	**የእርሶን መረጃ ለነዚህ ምክንያቶች እንጠቀማለን ወይም እናጋራለን:**
• የጤና እና ጥቅማጥቅሞችዎን ሰነዶች ኮፒ ይውሰዱ፡፡ • የጤና እና ጥቅማጥቅሞችዎን ሰነዶች ያስተካክሉ፡፡ • ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀ ግንኙነት ይጠይቁ፡፡ • መረጃዎን እንድንገድብ ይጠይቁን እንጋራለን፡፡ • የእርሳን መረጃ ያጋራናቸውን ዝርዝር(የተወሰኑትን ሳይጨምር) ያግኙ፡፡ • የዚህን የግል መብት ማስታወቂያ ያግኙ፡፡ • በእርሶ ቦታ ሆኖ የሚያስፈጸምሎትን አንድ ሰው ይምረጡ፡፡ • የግል መብትዎ የተጣሰ መሆኑን ካመኑ አቤቱታ ያቅርቡ፡፡ ➢ *ወደ ገፅ 2 ይለፉ ለበለጠ መረጃ.*	• ከቤተሰብዎ ወይም ከጓደኞችዎ ለሚቀርቡት የሽፋን ጥያቄዎች እንዴት ምላሽ እንደምንሰጥ፡፡ • የአደጋ መልሶ መቋቋሚያ እንዴት እንደምንሰጥ፡፡ እኛ አገልግሎታችንን ወይም የእርሶን መረጃ አንሸጥም ➢ *ወደ ገፅ 3 ይሂዱ ለበለጠ መረጃ.*	• የሚያገኙትን የጤና ጥበቃ አገልግሎት እንድንቆጣጠር ለማስቻል፡፡ • ድርጅታችንን ለማንቀሳቀስ፡፡ • ለጤና አግልግሎትዎ ለመክፈል፡፡ • የጤና እቅድዎን ለማስተዳድር፡፡ • የህብረተሰብ ጤናና ደህንነት ችግሮች ላይ እገዛ ለማድርግ፡፡ • ምርምር ለማካሄድ፡፡ • ህጉን ለማክበር፡፡ • ለአካል ወይም ለህብረ ህዋስ ጥየቄዎች ምላሽ ለመስጠት እና ከጤና መርማሪ እና ከቀብር ስንስርዓት ዳይሬክቴር ጋር አብረን ለመስራት፡፡ • የሰራተኞችን ማካካሻ፣ የህግ አፈፃፀም እና ለሌሎች የመንግስት ጥየቄዎች ምላሽ ለመስጠት፡፡ • ለክሶች እና ህጋዊ እርምጃዎች ምላሽ ለመስጠት፡፡ • የጥራት ማሻሻያ እድሎችን ለመለየት፡፡ ➢ *ወደ ገፅ 3 & 4 ይሂዱ ለበለጠ መረጃ፡፡*

የእርስዎ መብቶች

የጤና መረጃዎትን በተመለከተ የተወሰኑ መብቶች ይኖርዎታል፡፡ ይህ ክፍል የልዎትን መብቶች እና እኛ እርስዎን ለመርዳት ያሉብንን የተወሰኑ ኃላፊነቶች የሚገልፅ ነው፡፡

የጤና እና የጥቅማጥቅሞን ሰነድ ኮፒ ያግኙ

- የእርሶን ጤና እና ሰነዶችን እና ሌሎች ስለ እርስዎ እኛ ጋር ያሉ መረጃዎችን ለማየት ወይም ኮፒ ለማግኘት በፅሁፍ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ይህንን እንዴት ማድረግ እንዳለቦት ይጠይቁን፡፡
- አብዛኛውን ጊዜ የጤናዎን እና የጥቅማ ጥቅምዎን ሰነዶች ከጠየቁን ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድርሰ ኮፒውን ወይም ማጠቃለያውን እንሰጥዎታለን፡፡ አግባብነት ያለው እና ወጪን ያገናዘበ ክፍያ ልናስከፍሎት እንችላለን፡፡ ለእርስዎ መስጠት የሌሉብን የተወሰኑ ሰነዶች አሉ፡፡

የጤና እና የጥቅማ ጥቅም ሰነዶችዎን እንድናስተካክል ይጠይቁን

- የጤና እና የጥቅማ ጥቅምዎ ሰነዶች ስህተት ያለባቸው ወይም ያልተሟሉ ናቸው ብለው ካሰቡ እንድናስተካክል በፅሁፍ ሊጠይቁን ይችላሉ፡፡ ይህ ስለ እርስዎ ውሳኔ ለመስጠት የምንጠቀምባቸው አይነት ሰነዶችን የሚመለት ነው፡፡ ይህንን እንዴት እንደሚያደርጉ ይጠይቁን፡፡
- ለሚያቀርቡሉን ጥየቄ "የለም" ልንል እንችላለን ነገር ግን በ60 ቀናት ውስጥ ምክንያቱን በፅሁፍ እንገልፅሎታለን፡፡

ሚስጢራዊ ግንኙነት ይጠይቁን

- የእርስዎን በተወሰነ መንገድ (ለምሳሌ በቤት ወይም በቢሮ ስልክዎ) እንድንደውልዎ ወይም በሌላ አድራሻ የኢሜል መልክት እንድንልክልዎ ሊጠይቁን ይችላሉ፡፡
- ሁሉንም አግባብነት የላቸውን ጥያቄዎችን እንቀበላለን፡፡ እኛ አዎ ካላልን አደጋ ውስጥ እንደሚሆኑ ከነገሩን "አዎ" ማለት አለብን፡፡

የምንጠቀመውን እና የምናጋራውን እንድንገድብ ይጠይቁን

- የተወሰኑ የጤና መረጃዎችን ለህክምና ለክፍያ ወይም ለእንቅስቃሴአችን እንዳንጠቀም ወይም እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ፡፡
- እርስዎ በሚጠይቁን መስማት አይጠበቅብንም ምክንየቱም የእርስዎን የጤና እንክብካቤ ሊጎዳ የሚችል ከሆነ "አይሆንም" ልንል እንችላለን፡፡

መረጃ ያጋራናቸውን ዝርዝር ያግኙ

- የእርስዎን የጤና መረጃ እርስዎ ከጠየቁበት ቀን በፊት ለ6 ዓመታት ለማን እና ለምን እንዳጋራን ዝርዝሩን መውሰድ ይችላሉ፡፡
- ስለ ህክምና፣ ክፍያ፣ እና የጤና እንክብካቤ ስራዎች እና የተወሰኑ ሌሎች ይፋ አደራረጎች (ማንኛውም እርስዎ እንድናደርግሎት የጠየቁን አይነት) ካልሆነ በስተቀር ሁሉንም ይፋ አደራረጎች እናካትታለን፡፡ በየአመቱ ያለ ክፍያ ዝርዝሩን አንድ ጊዜ የምንሰጥ ሲሆን ነገር ግን በዛኑ ቀን 12 ወር ውስጥ ሌላ ተጨማሪ ቀጠየቁን አግባብነት ያለው እና ወጪና ያገናዘበ ክፍያ እናስከፍሎታለን፡፡

የዚህን የግል መብት ማስታወቂያ ያግኙ

- ምንም እንኳን በኤሌክትሮኒክስ ለመቀበል የተስማሙ ቢሆንም የዚህን ማስታወቂያ ኮፒ በወረቀት መውሰድ ይችላሉ፡፡ ወዲያውኑ በወረቀት ኮፒ እንሰጥዎታለን፡፡

እርስዎን ወክሎ የሚያስፈፅምሎትን አንድ ሰው ይምረጡ

- ለአንዱ ሰው የህክምና ውክልና ስልጣን ከሰጡ ወይም አንድ ሰው ለእርስዎ ህጋዊ አሳዳጊ ከሆነ የእርስዎን መብት ማስጠበቅ እና ስለ ጤና መረጃዎ ሊወሰን ይችላል፡፡
- ምንም አይነት እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ይህ ግለሰብ ስልጣኑን እንዳለ እና በእርሶ ቦታ ሆኖ ጉዳዩን ማስፈፀም እንደሚችል የምናረጋግጥ ይሆናል፡፡

መብትዎ የተጣሰ ሆኖ ከተሰማዎ አቤቱታ ያቅርቡ

የግል መብትሆ ተጥሷል ብለው ካሰቡ ወይም ጥየቄ ካለዎት፡

- የHCA የግል መብት ኦፊሰር በሚከተሉው ስልክ ቁጥር ያነጋግሩ
  1-844-284-2149 ጽሑፍ፡ HCA Privacy Officer,Health Care Authority,P.O. Box 42700,OLYMPIA WA 98504-2700. ወይም
- ለዩናይትድ ስቴት ጤናና ሰብዓዊ መብቶች የሲቪል መብቶች ፅህፈት ቤት በ200 Independence Avenue, S.W., Washington, D.C. 20201, ወይም 1-877-696-6775, ይደውሉ ወይም ቀጣዩን ድህረ ገፅ ይጎብኙ www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/complaints/፡፡
- ቅሬታ ስላቀረቡ በእርሶ ላይ ቂም አንይዝም፡፡

ምርጫዎችዎ

ለተወሰኑ የጤና ምርጫዎች እኛም ስለምናጋራቸው መረጃዎች የእርስዎን ምርጫ ሊነግሩን ይችላሉ፡፡ ከዚህ በታች በተገለፁት ሁኔታዎች የእርሶን መረጃ የምናጋራበትን መንገድ በተመለከተ ግልፅ የሆነ ምርጫ ካለዎት ፣ ይንገሩን ምን እንድናደርግልዎት ይንገሩን እና የእርስዎን መመሪያ እንከተላለን፡፡

በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ለእኛ ለመንገር መብቱንም ምርጫውንም አለዎት:

- ከቤተሰብዎ ፣ የቅርብ ጓደኛዎ ወይም በእርስዎ ጤና እንክብካቤ ክፍያ ውስጥ ተሳትፎ ላላቸው ሌሎች ማጋራት፡፡
- በአደጋ መልሶ ማቋቋሚያ መረጃ ማጋራት፡፡

ምርጫዎን ሊነግሩን ካልቻሉ ለምሳሌ አእምርዎ መወሰን የማይችል ከሆነ የእርሶን ጥቅም የበለጠ ያስጠብቃል ብለን ካመንበት የእርስዎ መረጃ ማጋራቱን እንቀጥላለን፡፡ በጤናና ደህንነት ላይ ከባድ እና አደገኛ ስጋት ለመቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የእርስዎን መረጃ ንናጋራ እንችላለን፡፡

ስለ አጠቃቀማችን እና ይፋ አደራረጋችን

የእርስዎን የጤና መረጃ በትክክል እንዴት እንደምንጠቀም እና እንደምናጋራ? የእርስዎን የጤና መረጃ በሚከተሉት መንገዶች በትክክል እንጠቀምበታለን ወይም እናጋራለን፡፡

እየወሰዱ ያለውን የጤና እንደክብካቤ ለመቆጣጠር

- የጤና መረጃዎን የህክምና እንክብካቤ ከሚያደርጉሎት ባለሞያዎች ጋር ልንጠቀም ወይም ልንጋራ እንችላለን፡፡

  ምሳሌ *አንድ ሀኪም ስለ እርሶ ይህክምና ምርመራ ውጤት እና ሊሰጥዎት ስለታቀደ የህክምና እንክብካቤ መረጃ ሲልክልን እኛ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ልናመቻች እንችላለን፡፡ ወይም እርስዎ በጥብቅ ስር ያሉ ህፃን ከሆኑ መረጃ ለህፃናት አስተዳደር እንልካለን፡፡*

ድርጅታችንን ለማንቀሳቀስ

- ድርጅታችንን ለማንቀሳቀስ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የእርሶን መረጃ ልንጠቀም እና ይፋ ልናደርግ እንችላለን፡፡
- ሽፋኑን እና የሽፋኑን ዋጋ እንደምንሰጥዎ ለመወሰን የዘረ መል መረጃ መጠቀም አይፈቀድልንም፡፡ ይህ የረጅም ጊዜ የጤና እንክብካቤ እቅድን አይመለከትም፡፡

  ምሳሌ *የጤና መረጃ ለእርስዎ የተሸለ አገልግሎት ለማዘጋጀት እንጠቀማለን፡፡*

ለጤና አገልግሎቶዎ ለመክፈል

- ሽፋን ለተሰጠ የጤና አገልግሎትዎ ክፍያ በሚፈፅሙበት ጊዜ የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም እና ይፋ ልናደርግ እንችላለን፡፡

  ምሳሌ *የቀዶ ህክምና ክፍያ ለማመቻቸት የእርስዎን መረጃ ለሀኪምዎ ልናጋራ እንችላለን፡፡*
- ቅሬታን ለመስማት አስተዳደራዊ ችሎት እዲቆምሎት ከፈቀዱ በችሎቱ ሂደት ላይ ሁል ጊዜ ስለእርስዎ ይፋ ማድርግ ይኖርብናል፡፡

የእርስዎን የጤና መረጃ ለሌላ እንዴት እንደምንጠቀም ወይም እንደምንጋራ? በሌሎች መንገዶች አብዛኛውን ጊዜ ለህብረተሰቡ ጤና አስተዋፅዎ ካለው ለህብረተሰብ ጤናና ለምርምር ለመሳሰሉት የእርስዎን መረጃ ለመጠቀም ወይም ለመጋራት ይፈቀድልናል ወይም ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህ አላማ የእርሰዎን መረጃ ከማጋራታችን በፊት ብዙ ህጋዊ መስረፈርቶችን ማሟላት አለብን፡፡ ለበለጠ መረጃ www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/understanding/consumers/index.html ይጎብኙ.

አጠቃቀም እና ይፋ አደራረጋችን

የህብረተሰብ ጤናና ደህንነት ችግሮችን ለመፍታት እገዛ ለማድረግ

- ስለ እርስዎ የጤና መረጃ ለሚከተሉት አላማዎች ልናጋራ እንችላለን፡
- በሽታ ለመከላከል፡፡
- የምርት ግብዓት ለመጠየቅ፡፡
- በህክምናዎች ላይ ጫና እንደሚያሳድሩ የተጠረጠሩ ሁኔታዎች ላይ ሪፖርት ለማቅረብ፡፡
- የተጠረጠረን ጥቃት፣ ማግለል ወይም የቤት ውስጥ ትንኮሳን ርፖርት ለማድረግ፡፡
- በማንኛውም ሰው ጤናና ደህንነት ላይ ከባድ ስጋት ለማስቀረት፡፡

ምርምር ለማካሄድ

- የእርስዎን መረጃ የጤና ምርምር ለማካሄድ ልንጠቀምበት ወይም ልናጋራ እንችላለን፡፡

ህግን ለማክበር

- የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንትን ጨምሮ የፌደራል የግል ህግን ማክበራችንን በማረጋገጥ መንግስት ወይም የፌደራል ህጉ ሲጠይቀን የእርስዎን የ ጤና መረጃ እናጋራለን፡፡

ለአካል እና ህብረ ህዋስ ልተሳ ጥያቄዎች ምላ ሽ ለመስጠት እና ከህክምና መርማሪ ወይም የቀብር ስነ ስርዓት ዳይሬክተር ጋር በጋራ ለመስራት

- የእርስዎን የጤና መረጃ ለአካል ግዢ ድርጅቶች ልናጋር እንችላለን፡፡
- ሞት ሲያጋጥም የእርስዎን የጤና መረጃ ለገናኙ ፣ ለመርማሪ ሀኪም እና ለቀብር ስነስርአት ዳይሬክተር ልናጋራ እንችላለን፡፡

የሰራተኞችን የካሳ ችግሮች፣ የህግ አፈፃፀም እና የመንግስት ሌሎች ጥየቄዎች ላይ ምላሽ ለመስጠት

- ስለ እርስዎ መረጃ ለሚከተሉት ልንጠቀም ወይም ልናጋራ እንችላለን፡
  - ለሰራተኞች ካሳ ጥያቄ፡፡
  - ለህግ አፈፃፀም አላማ ወይም ለህግ አስፈፃሚ ባለ ስልጣን፡፡
  - ለጤና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች ህጉ ለሚፈቅደው ተግባር፡፡
  - እንደ ወታደር፣ ብሄራዊ ደህንነት እና የፕሬዚዳንት ጥበቃ አገልግሎቶች በመሳሰሉት ልዩ የመንግስት አካላት፡፡

ለክስ ወይም ህጋዊ እርምጃ ምላሽ ለመውሰድ

- ለፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ ትእዛዝ ወይም ለምስክርነት ምላሽ ለመስጠት የእርስዎን የጤና መረጃ ልናጋራ እንችላለን፡፡

በተለየ ሁኔታ የሚጠበቁ መረጃዎች አሉ?

አዎ፣ የተወሰኑ አይነት መረጃዎች በዋሽንግተን ግዛት ወይም በፌደራል ህጎች ስር ልዩ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት የይፋ አደራረግ ተግባር በእንዲህ አይቶቹ መረጃ ላይ ማለትም በዋሽንግተን ግዛት ህጎች መሰረት ጥበቃ የሚደረግለት ምስጢራዊ ከ HIV ጋር የተያያዘ መረጃ፣ በዋሽንግተን ግዛት እና በፌደራል ህጎች ጥበቃ የሚደረግለት የአልኮል እና የእፅ ሱስ ህክምና መረጃ እና ጥበቃ የሚደረግለት የአምሮአዊ ጤና ህክምና መረጃ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

ኃላፊነቶቻችን

- ጥበቃ የሚደረግለትን ይህክምና መረጃዎን ሚስጢራዊንት እና ደህንነት እንድንጠብቅ ህጉ ያስገድደናል፡፡
- የእርስዎን የጤና መረጃ ሚስጢራዊነት እና ደህንነት ሊነካ የሚችል ጥፋት ከተፈጠረ ወዲያውኑ እናሳውቆታለን፡፡
- እኛ በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች እኛ የሚስጢር አጠባበቅ ተሞክሮዎችን መከተል እና እርስዎ ሲጠይቁ ኮፒውን ለእርስዎ መስጠት ይኖርብናል፡፡
- እርስዎ መጠቀም እንደምንችል በዕሁፍ ካላሳወቁን በስተቀር የእርስዎን የጤና መረጃ በዚህ ውስጥ ከተገለፀው አላማ ውጪ አንጠቀምም ወይም አናጋራም፡፡ እርስዎ ከፈቀዱልን እንችላለን፡፡ ነገር ግን ሀሳብዎን በመማንኛውም ጊዜ መለወጥ ይችላሉ፡፡ ሀሳብዎን ከለወጡ በዕሀፉ ይግለፁልን፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ ያለውን የፌደራል መንግስት ድህረገፅ ይጎብኙ www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/understanding/consumers/noticepp.html.

በዚህ ማስታወቂያ ቃሎች ላይ የሚደረግ ለውጥ

የዚህን ማስታወቂያ ቃሎች መቀየር ይምንችል ሲሆን ለውጡም ስለእርስዎ ባለን ማንኛውም መረጃ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ አዲሱን ማስታወቂያ የምንሰጥዎት ወይም ስለ እርሱ ወይም እንዴት ኮፒውን ማግኘት እንደሚችሉ እንነርዎታለን፡፡ የተሻሻለው ማስታወቂያ በድህረ ገፃችን ላይ የሚለጠፍ ሲሆን ከጠየቁን በኢሜል ልንልክልዎት ወይም ኮፒውን ልንሰጥዎት እንችላለን፡፡ ማስታወቂያው በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛል፡፡ ድህረ ገፃችነንን በ www.hca.wa.gov/pages/privacy.aspx ይጎብኙ.